# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير اورومو

Gaafa: 04/01/2018
Date: تاريخ

Lakk.: **024/stm-abo/2018**
No.: رقم

## ሰብዓዊ ሰቆቃዎችን ማስቆም እንጂ አሮጌን በአዲስ እስር ቤት መተካት መፍትሄ አይሆንም
## የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግላጫ

ከ27 ዓመት በፊት በወታደራዊ ሃይል ደርግን ከስልጣን ያስወገደው የወያኔ ኢህአዴግ ቡድን ላለፉት 27 ዓመታት የኢትዮጵያን ኢምፓየር እየገዛ ይገኛል። ህዝቦችም በወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ላይ እያካሄዱት ያለው ትግል ለዘመናት ስር ሰዶ ያለው የፖለቲካ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ እንዲበጅለት የሚጠይቅ ነው።

የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት ህዝቦች መብታቸው እንዲከበርላቸው በመጠየቃቸው፣ይህን የህዝቦች ጥያቄ በጠመንጃ አፈሙዝ ለማፈንና ብሎም ለመደመሰስ ላለፉት 27 ዓመታት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። ይሁን እንጂ የኢምፓየሪቷ ህዝቦች በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ለነጻነት፣ለብልጽግና ለሰላምና ለሐቀኛ ዲሞክራሲ ያደረገው ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ ወያኔ የሚያካሂደውን አፈና እየበጣጠሰ ይህን መንግስት ከውጭ መግፋት ብቻ ሳይሆን ውስጡ ገብቶ እያመሰው ይገኛል።

በመሆኑም ወያኔ/ኢህአዴግ ባሁኑ ወቅት ኢምፓየሪቷን ተቆጣጥሮ ሰላም አስከብሮ መግዛት ከማይችልበት ደረጃ እንዲደርስ ከማድረግ አልፎ በህዝቡ ትግል እርስ በርሳቸው እንዲናቆሩና እንደቀድሞው አብረው መጓዝ ከማይችሉበት ደረጃ እንዲደርሱ ማድረጉ በግልጽ እየታየ ነው። ከዚህም የተነሳ ባሁኑ ወቅት ፓርቲው እየወሰደ ያለው የማስመሰያ እርምጃ ስልጣን ላለመልቀቅ የተወሰደ እንጂ የህዝቦችን ጥያቄዎች የሚመልስ አይደለም።

ሶስት ሳምንታትን ያስቆጠረው የኢህዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ መግለጫ በሀገሪቷ ውስጥ የሚታየውን የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግር ለመፍታት ያለመ ሳይሆን ህዝቦችን የማታለልና በትግላቸው ላይ በመሳለቅ የበለጠ እልክ የሚያስገባቸውና ችግሮችን የሚያባብስ ነው።

ኢህአዴግ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች ውስጥ “የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ማዕከልን እንዘጋለን” የሚል ይገኝበታል። ለዚህም እንደምክንያት ያቀረበው ይህ የምርመራ ማዕከል በደርግ የአገዛዝ ዘመን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶችና ሰቆቃዎች ሲፈጸሙበት የነበሩ በመሆኑ እኛም በዚህ የወንጀል ምርመራ ማዕከል መጠቀማችን፣ ህዝቡ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖረው አድርጓል የሚል ነው። በዚህም ወያኔ/ኢህአዴግ ላለፉት 27 ዓመታት በሀገሪቷ ዜጎች በተለይም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲፈጽማቸው የነበሩትን ዘግናኝና አሰቃቂ ድርጊቶችን ለመካድና አድበስብሶ ለማለፍ ሞክሯል።

ኢህአዴግ የወንጀል ምርመራ ማዕከሉን እዘጋለሁ ይበል እንጂ ማዕከሉ ውስጥ የሚፈጸሙት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በሌላ አዲስ ተለዋጭ ማዕከል እንደሚቀጥልበትም አልሸሸገም። ከማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ማዕከል በተጨማሪ በወያኔ ወታደራዊ ካምፖች በሞላ አምባገነናዊነትን የሚቃወሙ ዜጎች የሚሰቃዩበት የማዕከሉ ቅርንጫፎች በብዛት እንዳሉ ይታወቃል። በተጨማሪም በየክልሉ በተለይም ትግራይ ውስጥ ይህን መሰል የስቆቃ መፈጸሚያ ማዕከሎች መኖራቸው አይካድም። ይህ ሁሉ እየታወቀ “የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ” እንዘጋለን ማለቱ እስካሁን በፈጸሙት ወንጀል ላይ ወንጀል ከመፈጸም ባሻገር በፈሰሰው የንጹሃን ደም መቀለድ ይሆናል።

በተጨማሪም ማዕከላዊ ይዘጋል፣ተዘጋ ተብሎ የሚታልፍ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። በዚህ ማዕከል በዘመነ ደርግ ለ17 ዓመታት በሰው ልጆች ላይ ምን አይነት ወንጀሎች ተፈጸሙ? በዘመነ ወያኔ ኢህአዴግ ከ26 ዓመታት በላይ ምን አይነት የሰቆቃ ድርጊቶች ተፈጸሙ? ለዚህስ ተጠያቂው ማነው? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይገባቸዋል።

ሌላው በኢህአዴግ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለህዝቦች የተገለጸው ውሳኔ “ብሄራዊ መግባባትን ለማስገኘት ከፖለቲካ እስረኞች ገሚሶቹን እንፈታለን” የሚለው ነው። ይህም ህዝቦችን ለማታለል በማይተገበር ውሳኔ በተስፋ ለማቆየትና ፋታ ያስገኝልኛል በሚል እምነት የተነገረ እንጂ ምንም እርባና የሌለው መሆኑን ከመግለጫው መረዳት ይቻላል። በድርጅቶች አባልነትና ደጋፊነት ብቻ በወያኔ የአገዛዝ ዘመን በሞላ ወደ እስር ቤት የተጋዙትና እየተጋዙ ያሉ ዜጎች በአስር ሺህዎች ይቆጠራሉ። ገሚሶቹ ያለ ምንም ፍርድ ሌሎች ደግሞ የሞትና የእድሜ ለክ እስራት ተፈርዶባቸው በእስር ቤት እየማቀቁ ይገኛሉ። ከነዚህ ታሳሪዎች ውስጥ እነማን? ስንቶቹ? ከየትኛው እስር ቤት? መቼ ይፈታሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መግለጫው ምላሽ አይሰጥም። ከዚህም በተጨማሪ፣ በመላው ሀገሪቱ በማይታወቁ በተለይም ትግራይ ውስጥ በሚገኙ እስር ቤቶች የሚማቅቁ እስረኞች እጣ ፈንታ ምንድን ነው? ለሚለው የተገለጸ ነገር የለም። ስለዚህ “የፖለቲካ እስረኞችን እንፈታለን” የሚለው የኢህአዴግ ውሳኔ ሓቅ የጎደለውና ተጨባጭ የማይሆን ለህዝቦች መሰረታዊ ጥያቄም መልስ ሊሆን የሚችል አይደለም። ላለፉት 26 ዓመታት በስልጣን ላይ የነበሩትም ሆኑ በስልጣን ላይ ያሉት የአገዛዙ ባለስልጣናት ይህን መሰል

የማታለያ ውሳኔ በማሳለፍ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ አይችሉም።

ባጠቃልይ በወያኔ ኢህአዴግ እየተወሰደ ያለው እርምጃና እንቅስቃሴው በተጨባጭ እየታየ ያለውን የፖለቲካ፣ኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች የማይፈታ፣ የኦሮሞ ህዝብ ላነሳቸው የሙብት ጥያቄዎች መፍትሄ ለማስገኘት ፍላጎት፣ ችሎታና ዝግጁ ኣለመሆኑን፣ እንዲሁም በህዝቦች ትግል ከስልጣን እስካልተውገደ ድረስ አገዛዙን ለማስቀጠል መወሰኑን የሚያረጋግጥ ነው። ስለሆነም መላው የኢምፓየሪቷ ህዝቦች በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ወያኔ/ኢህአዴግ ስልጣን ላይ በመቆየት እስራት፣ግድያና ዘርፋውን ለማስቀጠል ባስተላለፋቸው የማታለያ ውሳኔዎች እንዳይዘናጋና ትግሉን እንዲያፋፋም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጥሪውን ያስተላልፋል።

ያለው ብቸኛ ምርጫ ለእውነተኛ ነጻነት፣ ፍትህና ለሐቀኛ ዲሞክራሲ ህዝቦች በሁሉም አቅጣጫ እያደረጉ ያሉትን ትግል የበለጠ በማፋፋም በጠመንጃ አፈሙዝ በህዝቦች ጫንቃ ላይ ተቆናጦ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም የሚፍጨረጨረውን የወያኔ መንግስት ማስወገድ መሆኑን አነግ በድጋሜ ያሳስባል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ !

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር
ጥር 04 ቀን 2017 ዓ፡ም